## ጋዜጣዊ መግለጫ

የካቲት 15 ቀን 2016

EHRDC

# በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታሰሩ የመብት ተሟጋቾች ፍትሕ ይሻሉ!

**የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ መንግስት በወሰደው እርምጃ ጋዜጠኞችን ጨምሮ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች ለጅምላ እስር ተዳርገዋል።**

በአማራ ክልል የተቀሰቀሰውን ውጥረት ተከትሎ ጋዜጠኞችን ጨምሮ በርካታ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ለእስር መዳረጋቸው ይታወቃል። ድርጅታችን፤ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል ጉዳያቸውን ሲከታተል እና ፍትሕ እንዲያገኙ ድምጹን ሲያሰማ የቆየ ቢሆንም ያደረግናቸው ውትወታዎች እና ያቀረብናቸው ምክረ ሃሳቦች ምላሽ ሳያገኙ ቀርተዋል። ይሁንና በክልሉ ውስጥ ያለው ውጥረት ወደ ግጭት ማምራቱን ተከትሎ ለ6 ወራት የቆየ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሃምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ታውጇል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ መንግስት በወሰደው እርምጃ ጋዜጠኞችን ጨምሮ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች ለጅምላ እስር ተዳርገዋል። ማዕከላችን የሰብአዊ መብት ተሟጋቾቹ ለእስር መዳረግ የለባቸውም ብሎ ቢያምንም የአዋጁ የስድስት ወር ጊዜ ገደብ ሲያልቅ ግን በነጻ ይፈታሉ የሚል ተስፋ ነበረው። ቢሆንም አዋጁ ድጋሚ ለአራት ወራት መራዘሙ እስረኞቹ እጅግ አስቸጋሪ በሆነው የእስር ሁኔታ ውስጥ እንዲቆዩ እና ፍትሕ የሚያገኙበትንም እድል የጠበበ እንዲሆን አድርጎታል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠውን በሚኖሩበት አካባቢ የመታሰር፣ በቤተሰቦች እና በሕግ አማካሪዎቻቸው የመጎብኘት መብቶቻቸው አለመከበር ለከፋ እንግልትና ለተለያዩ የመብት ጥሰቶች እንደዳረጋቸው ማዕከላችን ባደረገው ክትትል አረጋግጧል። ከዚህ ጋር በተገናኘ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብታቸው በመጣሱ በፍርድ ሂደት የማለፍ እና በነጻ ችሎት ተዳኝቶ ፍትሕ የማግኘት መብቶቻቸውንም እንዲያጡ ተደርገዋል። ታሳሪዎቹ በእስር የሚገኙበት እጅግ አስቸጋሪ ሥፍራም በጤናቸው ላይ እያደረሰባቸው ካለው ከፍተኛ ጉዳት ባሻገር እጅግ ከፍተኛ ለሆነ የስነ-ልቦና ጫና እንዳጋለጣቸው ከቤተሰቦቻቸው ባገኘነው መረጃ ለማረጋገጥ ችለናል።

የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ሀገራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚያውጁበት ወቅት አዋጁ የተመጣጣኝነት፣ ህጋዊነት፣ ቅቡልነት እና አስፈላጊነት መርሆችን የተከተለ መሆን እንዳለበት ይደነግጋሉ። ይህም ማለት በልዩ ሁኔታ የተጋረጠውን ችግር ብቻ የሚፈታ፣ የህግ መሰረት ያለው፣ ግልጸኝነት የሚታይበት፣ ተጠያቂነትን ያረጋገጠ እና ገደቦች በጥንቃቄና በጠባቡ የተተረጎሙ መሆን እንዳለባቸው ያሳየናል። ይሁንና በኢትዮጵያ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከነዚህ አለም አቀፍ የስነ-ስርአት መርሆች አንጻር ሲገመገም ብዙ ጉድለቶች የሚታዩበት እና ለህግ አስፈጻሚው አካል ያልተገደበ ስልጣን በመስጠት ተመጣጣኝ ባልሆነ መልኩ ጋዜጠኞችን ጨምሮ በሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ ያልተገባና የጅምላ እስር እንዲደረግ ከለላ እየሰጠ ይገኛል።

# ጋዜጣዊ መግለጫ

EHRDC

የካቲት 8 2016 ዓ.ም በእሥር ቤቱ በደረሰው የአውሎ ንፋስ አደጋ የመመገቢያ አዳራሹ ላይ ጉዳት ማድረሱን የካቲት 9 ቀን 2016 ዓ.ም የፌደራል ፖሊስ ቃል አቀባይ አቶ ጄላን አብዲ ከአሜሪካ ድምጽ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠየቅ አረጋግጠው ለተጎጂዎች አስፈላጊው ህክምና የተደረገላቸው መሆኑን አክለው ገልጸዋል። ይህ አስከፊ አደጋ በተጎጂዎች ላይ ሊደርስ የቻለው በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በሕግ ጥላ ሥር ለዋሉ ሰዎች መደረግ የሚገባቸውን መሠረታዊ ጥበቃዎችና ጥንቃቄዎች ያላሟላ፤ እንዲሁም በመደበኛ እሥር ቤትነት የማይታወቅ ሥፍራ በመሆኑ ነው። በመሆኑም መንግስት በሕገ መንግሥቱ እና አገሪቱ ፈርማ ባጸደቀችው አለም አቀፍ ስምምነቶች በሕግ ጥላ ሥር ለዋሉ ሰዎች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያደርግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች እንዲያመቻች እንጠይቃለን፤

1. ታሳሪዎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ በአፋጣኝ እንዲያጤነው እና በዚህ ሥፍራ በእስር ላይ የሚገኙ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾችን ጨምሮ ሌሎች ታሳሪዎችን የተሻለ ህክምና፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመቆያ ሥፍራ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር የሚገናኙበትንና በአስቸኳይም ፍርድ ቤት ቀርበው የተፋጠነ ፍትሕ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው፤
2. ጋዜጠኞችን ጨምሮ ለመብቶች ተሟጋቾች አስፈላጊውን የህግ ከለላ እንዲሰጥና ያለ አግባቡ የታሰሩ የመብት ተሟጋቾችን ከእስር እንዲፈታ እና በእስር ላይ በሚቆዩበትም ወቅት መሰረታዊ መብቶቻቸውን እንዲያከብር ማዕከሉ ይጠይቃል።

የካቲት 15 ቀን 2016

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጲያ